# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅ ምንጭ፡-** IJA, IJA-RA, IKA, IKA-RA, IKB-RA, IKC-RA, IOE-RA, IOE-RB, JFA, JFA-RA, JGA-RB, KLA, KLA-RA

**ኃላፊነት የሚመለከተው ቢሮ፡-** Office of Deputy Superintendent of Schools, Office of School Support and Well-being, Office of the Chief Academic Officer, Office of Strategic Initiatives, Shared Accountability

## የተማሪ በትምህርት ላይ መገኘት/ክትትል

I. **ዓላማ**

ከትምህርት መቅረት እንደሚመዘገብ እና በምክንያት የመቅረት ሃላፊነት-ተጠያቂነት

በሜሪላንድ ህግ ኮድ (COMAR) ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት በመደበኛነት በትምህርት ላይ የመገኘትን ባህርይ ለማዳበር፣ ክትትል ለማድረግ፣ እና ትምህርትን የመከታተል ልምድን ለማሻሻል ተማሪዎችን ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ክትትል የሚደረግበትን ሂደት ለመግለጽ

II. **ትርጓሜ**

ህጋዊ መቅረት ማለት COMAR 13A.08.01.03 ላይ እንደተጠቀሰው ተማሪ ከት/ቤት የሚቀርበትን ሁኔታ የሚገልፅ ነው።

III. **ቅደም-ተከተል**

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የድርጊት መርኖች

የት/ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ (OSSWB) ከስትራቴጂክ ኢንሼቲቭ ቢሮ እና ከሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች እና የውጭ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር –

1. በትምህርት ገበታ ላይ በመደበኛነት የመገኘትን አስፈላጊነት እንዲገነዘቡ የተማሪዎችን፣ የተንከባካቢዎችን እና የማህበረሰብ አባላትን ግንዛቤ ማሳደግ፣

2. በትምህርት ገበታ ላይ በመደበኛነት የመገኘትን ሁኔታ በመደበኛነት መረጃ ሪፖርት ማድረግና መተንተን ፣ እና

3. በመደበኛነት ትምህርት ቤት መከታተልን ለመደገፍ የተነደፉ ጣልቃገብነቶችን በቀጣይነት ማዳበር እና መተግበር።

B. ሁሉም ት/ቤቶች

1. እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ለማሳደግ የተዋቀሩ ፕሮቶኮሎችን ያዘጋጃል –

a) በተቆራረጠ ሁኔታ በትምህርት ላይ የመገኘትን መረጃ በየጊዜው መገምገም፣

b) ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር ግንኙነትን ማጠናከር እና እንደአስፈላጊነቱ ማበረታቻዎችን መስጠት፣

c) በትምህርት ገበታ ላይ በመደበኛነት ለመገኘት እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ዋና መንስኤ ትንተና ማድረግ፣ እና

d) እንቅፋት በሚሆኑ መንስኤዎች ላይ የታለመ ጣልቃገብነቶችን ተግባራዊ ማድረግ።

2. ትምህርት ላይ የመገኘት ሁኔታዎችን መመዝገብ እና ሪፖርት ማድረግ

a) የሜሪላንድ የተማሪዎች መዛግብት ሲስተም መመሪያ ከዚህ ጋር በአባሪነት ተካቷል።

b) እያንዳንዱ የክፍል አስተማሪ የተማሪዎችን ክትትል የመመዝገብ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት። መምህራን የተማሪዎችን መገኘት/አለመገኘት በቀጥታ በኦንላይን የመቆጣጠሪያ ዘዴ ይመዘግባሉ። ሲስተሙ የተመዘገበበትን ቀን፣ ሠዓት፣ እና መረጃ መዝጋቢውን ሰው ይገልጻል።

c) የኤሌክትሮኒክ ሲስተም መጠቀም በማይቻልበት ጊዜ፣ የስም ዝርዝር የያዘ መዝገብ/ሮስተር መጠቀም ይቻላል። እነኚህ ሠነዶች የትምህርት ዓመቱ እስከሚያልቅ ድረስ በት/ቤት ይቀመጣሉ። በትምህርት አመቱ መጨረሻ ላይ፣ በመዝገብ/ሮስተር ላይ የተያዙት ሰነዶች ለኦዲት አገልግሎት ለተጨማሪ ሶስት አመታት መቀመጥ ስላለባቸው ወደ ማእከላዊ የመረጃ ቋት ይላካሉ።

d) የእያንዳንዱ ተማሪ በየእለቱ ትምህርት ቤት የመገኘት ሁኔታ በተማሪዎች የመረጃ ቋት/መዝገብ በኤሌክትሮኒክ ሲስተም ተመዝግቦ ይያዛል።

e) OSSWB በተማሪዎች የመረጃ ሲስተም ውስጥ ያሉትን ሪፖርቶች በመጠቀም ትክክለኛነቱን ይፈትሻል።

f) ትምህርት ቤት ለመግባት ተመዝግበው በሴፕቴምበር ወር ት/ቤት ሪፖርት ያላደረጉ ተማሪዎች ሁኔታቸው ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ መወሰድ አለበት።

   (1) በሴፕቴምበር ወር ትምህርት ቤት ለመከታተል ተመዝግበው ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎች ት/ቤት ለመምጣት ጥረት አድርገው ያልቻሉበትን ምክንያት የሚያረጋግጥ አሳማኝ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ በሴፕቴምበር 30 ከት/ቤት እንዲሠረዙ እርምጃ መወሰድ አለበት።

   (2) የሰነድ መስፈርቶችን በሚመለከት የሜሪላንድ የተማሪዎች መዝገብ ቋት መመሪያ ውስጥ ተካቷል።

g) በተከታታይ 10 የትምህርት ቀናት ያለህጋዊ ፈቃድ ከት/ቤት የቀሩ ተማሪዎች በሜሪላንድ የተማሪዎች መዝገብ ቋት/ሲስተም መመሪያ ላይ በተዘረዘረው መሰረት መውጣት አለባቸው።

h) የጋራ ተጠያቂነት፣ኃላፊነት ቢሮ የክትትል ሂደት ትክክለኛነት እና ታማኝነትን በሚመለከት ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት ቤቶች ለመለየት የተሳትፎ ናሙናዎችን ይመረምራል። የጋራ ተጠያቂነት፣ኃላፊነት ቢሮ–

(1) MCPS የተማሪዎች መዝገብ አያያዝ መመሪያ ላይ ያሉትን የመዝገብ አያያዝ መስፈርቶች ጥራት እንዲኖራቸው እና ወቅቱን የጠበቁ እንዲሆኑ በየአመቱ ያለማቋረጥ እያሻሻለ ለሁሉም መዝጋቢዎች ይሰጣል፣ እና

(2) MCPS የተማሪ መዝገብ ያዢ መመሪያ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎችን ት/ቤት የማይገኙ ተማሪዎችን ጭምር መከተል ያለባቸውን ሂደቶች በሰራተኞች ስልጠና ወቅት ክለሳ የተደረገባቸው ጭብጦች መታወቅ አለበት።

i) አጠቃላይ የተማሪ ከትምህርት ቤት የመቅረት ብዛት (ህጋዊ እና ህገወጥ መቅረቶችን ጨምሮ) በሪፖርት ካርዱ ላይ ይመዘገባል።

3. ጣልቃ ገብነት

a) ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ፣ ከትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጋር በመተባበር፣ ከት/ቤት የሚቀሩትን ተማሪዎች ሁኔታ ለመከታተል የት/ቤቱን የአሰራር ቅደምተከተል ያዘጋጃል፣ ከት/ቤት የሚቀሩትን ተማሪዎች የክትትል ስልት እንዲፀድቅ በየአመቱ ለሚመለከተው ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ጁላይ 1 ያቀርባል፤ እንዲሁም ተቀባይነት ያገኘውን የክትትል ስልት በእያንዳንዱ የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለተማሪዎች ያሰራጫል።

b) የግለሰብ ተማሪ ከትምህርት የመቅረት መረጃ ሥር የሰደደ መሆኑ ሲታወቅ፣ ያለማቋረጥ ት/ቤት ያለመገኘቱ(ቷ)ን ወደ – ማስተላለፍ ያስፈልጋል

(1) መሠረታዊ ምክንያቶቹ ትንተና ተደርጎባቸው የተጠናከረ የችግር አፈታት ትብብር እንዲደረግ ለት/ቤት ደህንነት ቡድን (SWBT) ማሳወቅ፣ እና

(2) ትምህርት ቤት ስለመገኘት የሚደረጉ የተቀናጁ ጣልቃገብነቶች የተቀመጠውን የአሠራር ሂደት በመከተል ተመዝግበው ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

c) ከትምህርት ቤት የመቅረት ሁኔታ ሥር የሰደደ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቱ መሠረታዊ መንስኤዎቹን በመተንተን በትምህርት ቤት መገኘት በት/ቤት የማሻሻያ እቅድ ውስጥ ይካተታል። ትምህርት ቤቶች ባህላቸው እና የት/ቤቱ ሁኔታ ለሁሉም ተማሪዎቻቸው በትምህርት ላይ መገኘትን የሚያበረታታ ወይም የማያበረታታ መሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

C. አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (መዋዕለ ሕፃናት ጭምር)

1. በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ርእሰ መምህራን/ተወካዮች በማንኛውም ቀን ልጆቻቸው በማንኛውም ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት በሚኖርባቸው ጊዜ ወላጆች/አሳዳጊዎች ለትምህርት ቤቱ እንዲያሳውቁ መግለጽ አለባቸው።

2. በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጆች ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ልጆቻቸውን ከትምህርት ቤት እንደሚቀሩ ለሚመለከተው ት/ቤት ቀደም ብለው ካላሳወቁ፣ በተቻለ መጠን በእያንዳንዱ የመጀመሪያ መቅረት እስከ 12:00 ሰአት ድረስ ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለልጃቸው

ከት/ቤት መቅረት እንዲያውቁ ይገለጽላቸዋል።

3. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ህጋዊም እና ህገወጥ በሆነ ምክንያት ከመጠን በላይ ከትምህርት ቤት የሚቀሩ ከሆነ እና/ወይም ዘግይተው የሚመጡ ከሆነ፣ተገቢው የጣልቃገብነት እርምጃ እንዲወሰድ ወደሚመለከተው ሊመሩ ይችላሉ። በርእሰ መምህሩ/ተወካዩ ውሳኔ፣ በተደጋጋሚ ከት/ቤት የሚቀሩ ተማሪዎች መደበኛ የትምህርት ክትትልን ለማዳበር የተነደፉትን ከፍተኛ የጣልቃገብነት እርምጃ እንዲወሰድ ወደሚለከታቸው ሰራተኞች እና/ወይም የውጭ ኤጀንሲዎች ሊመሩ ይችላሉ።

D. የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች

1. በህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ ምክንያት ከመጠን በላይ መቅረት የሚያበዙ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እና/ወይም አርፋጆች አግባብነት ወዳለው ጣልቃ-ገብ ትግበራ እንዲተላለፉ ሊደረግ ይችላል።

2. በርእሰ መምህሩ/ተወካይ ውሳኔ፣ አዘውትረው የመቅረት ሁኔታን ያሳዩ ተማሪዎች መደበኛ የትምህርት ክትትል እንዲያደርጉ ለማሻሻል የተነደፉትን ከፍተኛ ጣልቃገብነት ለመተግበር ወደ ተገቢ ሰራተኞች እና/ወይም የውጭ ኤጀንሲዎች ሊመሩ ይችላሉ።

3. አምስት ቀኖች ወይም ከዚያ በላይ ከት/ቤት ያለፈቃድ የቀሩ ተማሪዎች ከት/ቤት ቀሪ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣቸዋል።

E. ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

1. በህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ ምክንያት ከመጠን በላይ መቅረት የሚያበዙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ተገቢ ወደ ሆነው ማስተካከያ እንዲሄዱ ሊደረግ ይችላል። የት/ቤት ካውንስለር ተማሪዎች የቀሩበትን ምክንያት ለማረጋገጥ እና ተገቢ የሆነ ጣልቃ-ገብ እርምጃ ለመወሰን ከተማሪው(ዋ) እና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ምክክር ያደርጋል/ታደርጋለች።

2. በርእሰ መምህሩ/ተወካዩ ውሳኔ፣ ዘወትር የመቅረት ሁኔታን ያሳዩ ተማሪዎች መደበኛ የትምህርት ክትትል እንዲያደርጉ ለማሻሻል የተነደፉትን ስልቶች ለመተግበር ለከፍተኛ ጣልቃገብነት ወደ ተገቢ ሰራተኞች እና/ወይም የውጭ ኤጀንሲዎች ሊመሩ ይችላሉ።

3. የትምህርት ቤት ካውንስለሮች/የአስተዳደር ቡድኖች የተማሪዎችን በትምህርት ቤት የመገኘት ሁኔታ ለማሻሻል ትምህርት ቤት የመገኘት ጣልቃ ገብነት እቅድ (AIP) ሊጠቀሙ ይችላሉ።

   a) እያንዳንዱ ተማሪ ስለሚወስዳቸው ኮርሶች MCPS ቅጽ 560-26B በመጠቀም የሚዘጋጀው ትምህርት የመከታተል-ጣልቃገብነት እቅድ (AIP)፣ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብቻይዘጋጃል። የተማሪን የትምህርት ክትትል እና አካደሚያዊ ሥራ ለማሻሻል በተማሪው(ዋ) እና/ወይም በሠራተኛ አማካይነት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች እና ስትራቴጂዎች በቅጹ ላይ ተቀምጠዋል።

   b) ርእሰመምህሩ(ሯ) የተዘጋጀውን AIP ከተመከተ(ች) በኋላ ይፈርምበታል/ትፈርምበታለች።

   c) AIP በመተግበር ላይ እያለ፣ የተገኘውን መሻሻል ለመወሰን ርእሰ መምህሩ(ሯ) በሴሚስተሩ ውስጥ በሙሉ የተማሪው(ዋ)ን ትምህርት ላይ የመገኘት ግምገማ ይመራል።

IV. በምክንያት መቅረት

A. COMAR ላይ የተጠቀሱ "ህጋዊ መቅረቶችን" MCPS ፈቃድ የሚሰጠው በሚከተለው ሁኔታ ነው፡-

1. የቅርብ ዘመድ ከሞተ

2. የተማሪ መታመም እና የደህንነት ስጋት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በትምህርት ላይ በብቃት ለመሳተፍ እንዲችሉ አካላዊ፣ ስሜታዊ እና ስነ ልቦናዊ ደህንነት እንደሚያስፈልጋቸው ይገነዘባል። ትምህርት ቤቶች ተማሪው(ዋ) አካላዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ደህንነትን በሚደግፉ ተግባራት ላይ ለመሠማራት፥ ወይም በህመም ምክንያት የቀረ(ች) ከሆነ የተማሪው(ዋ)ን መቅረት ምክንያታዊ አድርገው ይቀበላሉ።

a) በዚህ ደንብ መሰረት ህጋዊ የሆነ መቅረትን የሚያካትቱ የደኅንነት እንቅስቃሴ ተግባራት ተማሪው(ዋ) ወደ ትምህርት መከታተል እንዲመለስ/እንድትመለስ የሚረዱ አወንታዊ የአካል እና/ወይም የአእምሮ ጤናን የሚደግፉ ፕሮግራሞች ወይም ቴክኒኮች ተደርገው ይወሰዳሉ።

b) አንድ ተማሪ የተደጋገመ ወይም ለረዥም ጊዜ ከትምህርት ቤት የቀረ(ች) ከሆነ፣ ርእሰ መምህሩ የተማሪው(ዋ)ን ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ የሆነ ተማሪ የቀረ(ች)በትን ምክንያት ፈቃድ ካለው የጤና ባለሙያ ማስረጃ እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል። ከጤና ባለሙያ የተሰጠ ማስረጃ ከሌለ በተራዘመ የስነ-ልቦና ደህንነትን ምክንያት መቅረታቸውን ለማረጋገጥ ቤተሰብን የሚረዱ የማህበረሰብ አጋር ኤጀንሲዎች ወይም የተማሪን መቅረት የሚያውቁ የት/ቤት ሰራተኞች የጽሑፍ ማስረጃ በመስጠት ሊረዱ ይችላሉ።

c) MCPS ስለ ትምህርት ቤት እና የማህበረሰብ ስነምግባር ጤና ጠቃሚ ሪሶርሶችን/ግብዓቶችን በሚመለከት ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች መረጃ መስጠት አለበት። ይህ አይነት መረጃ የተማሪው(ዋ) መቅረት በባህሪ የጤና መቃወስ ምክንያት መሆኑን ለትምህርት ቤታቸው ለሚያሳውቁ ተማሪዎች እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎችም ይሰጣል።

3. ከእርግዝና ወይም ከወላጅነት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች

a) ትምህርት ቤቶች ከእርግዝና ወይም ከወላጅነት ጋር በተያያዙ ሁኔታዎች ምክንያት ሁሉንም የተማሪ መቅረት በምክንያታዊነት ይቀበላሉ፣ ይህም በምጥ ጊዜ፣ በሚወልዱበት ጊዜ፣ ለማገገም እና ለቅድመ ወሊድ እና ድህረ ወሊድ የህክምና ቀጠሮዎችን ይጨምራል፡-

(1) ተማሪ(ዋ)ው ልጅ ከተወለደ በኋላ ለወላጅነት እንክብካቤ ቢያንስ 10 ቀናት መቅረት ትችላለች/ይችላል፣

(2) በህመም ወይም በተማሪ(ዋ)ው ልጅ የህክምና ቀጠሮ ምክንያት ከወላጅነት ጋር የተያያዙ መቅረቶች፣ በትምህርት አመት እስከ አራት ቀናት የሚደርስ መቅረትን ጨምሮ ትምህርት ቤቱ ከልጁ ፈቃድ ያለው/ያላት የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ማስረጃ መጠየቅ አይቻልም፤ እና

(3) በእርግዝና ወይም በወላጅነት ምክንያት ወይም ከቤተሰብ ህግጋት ጋር የሚገናኝ፣ ጉዲፈቻን ጨምሮ፣ የልጅ አሳዳጊነት እና ጉብኝት ማናቸውም ህጋዊ በሆነ ቀጠሮ ምክንያት መቅረት

b) ትምህርት ቤቶች አንድ ተማሪ በእርግዝና ምክንያት ወይም ልጅ ለመውለድ ሆስፒታል ከገባች በኋላ ለተማሪዋ ህክምና ከሚሰጥ ፈቃድ ያለው የጤና ባለሙያ ማስረጃ ሊያስፈልግ ይችላል፣ይህ አይነት የህኪም ማስረጃ የሚያስፈልገው ከሌሎች ሆስፒታል ከሚገቡ ተማሪዎች ሁሉ የሚጠየቅ ከሆነ ብቻ ነው።

4. የፍርድ ቤት ጥሪ/ቀጠሮ

5. አደገኛ የአየር ሁኔታ ሁኔታዎች ማለት፥ ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ወደ ቤት በሚጓዙበት ጊዜ የተማሪዎችን ጤንነት እና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ነው።

6. በትምህርት ቤቱ የተፈቀደ ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚያደርገው ሥራ፣ የአካባቢው የትምህርት ሥርዓት፣ ወይም የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት ያፀደቀው ወይም የሚደግፈው ሥራ፣ በአካባቢው የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ወይም የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር/ተወካይ የተማሪዎችን ከትምህርት ቤት መቅረት እንደበቂ ምክንያት የሚወስደው ነው። ርዕሰ-መምህር/ተወካይ እንደ ህጋዊ መቅረት አድርጎ መቀበል ያለበት በተለያዩ ተግባራት ወይም የስራ ሁኔታዎች ምክንያት ከአምስት የትምህርት ቀናት አስቀድሞ በተማሪው(ዋ) በወላጅ/በሞግዚት/ብቃት ባለው ወይም ብቃት ባላት ተማሪ በጽሑፍ ከጠየቀ እንደ ህጋዊ መቅረት ተደርጎ ይወሰዳል፤ ይህም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ያካትታል፦

a) የኮሌጅ ካምፓሶችን ለመጎብኘት እና በኮሌጅ ዝንባሌ መርሃ ግብሮች ላይ ለመሳተፍ (ስላለው ገደብ የአካባቢ ተማሪዎች መመሪያ ይመልከቱ)

b) ከወደፊት የሥራ ቀጣሪዎች ጋር ለቃለ-መጠይቅ የተያዘ ቀጠሮ

c) በትብብር ትምህርት ፕሮግራም ያልተመዘገቡ ተማሪዎች ለአጭር-ጊዜ የሙሉ ጊዜ ሥራ ላይ ከተመደቡ

7. ኃይማኖታዊ በዓል ለማክበር

8. የስቴት አስቸኳይ ሁኔታ

9. እገዳ

10. MCPS የማጓጓዣ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለተፈቀደላቸው ተማሪዎች መጓጓዣ እንዳይሰጥ የሚከለክሉ ሁኔታዎች። ይሄ እርምጃ በዲስፕሊን ቅጣት ምክንያት ከ MCPS የመጓጓዣ አገልግሎት መታገድን አይጨምርም

11. ከትምህርት ቤት የሚያስቀር በቂ የሆነ ምክንያት እንደሆነ የታመነበት ሌላ አስቸኳይ ሁኔታ መሆኑን የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ወይም ተወካይ ሲበይን

B. ከት/ቤት የመቅረት ሁኔታው ህጋዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ስለመወሰን።

1. ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ሌሎች ምክንያቶች እንደ ህጋዊ የመቅረት ምክንያት መሆናቸውን በርእሰ መምህር ውሳኔ መፍቀድ ይቻላል። በመሠረቱ፣ ለቤተሰብ ጉዞ የሚቀርቡ ጥያቄዎች እንደ ህጋዊ መቅረት አይቆጠሩም (በተጨማሪ ክፍል III.A.5.e ይመልከቱ)።

   የሚከተለውን ግምት ውስጥ በማስገባት በርእሰ መምህሩ/ተወካዩ ውሳኔ የተማሪ ከትምህርት ቤት መቅረት እንደ ህጋዊ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

   a) የተማሪን ከትምህርት ቤት መቅረት ለማጽደቅ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የተማሪው(ዋ) መቅረት በተማሪው(ዋ) አካደሚያዊ እድገት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተፅእኖ እና የትምህርት ማካካስ አማራጮችን አስመልክቶ ከተማሪው(ዋ) መምህር(ራን) የሚሰጥ ምክረሃሳብ።

   b) ተማሪው(ዋ) እስከ ዛሬ የተከማቸበ(ባ)ት ህጋዊ እና ህገ-ወጥ የመቅረት ብዛት።

   c) ትምህርት ላይ ለመገኘት አለመቻል አላማው ወይም ልዩ ምክንያት።

   d) ከትምህርት ቤት የቀረ(ች)በት ጊዜ ብዛት

2. በበቂ ምክንያት የሚሆን ከትምህርት ቤት መቅረትን ግምት ውስጥ ለማስገባት አስቀድሞ የፈቃድ ጥያቄ መቅረብ አለበት።

3. ት/ቤት ሙሉ ጊዜ ት/ቤት ለተከታተሉ ተማሪዎች ሽልማት መስጠት ሲያስፈልግ በኃይማኖታዊ ምክንያት የመቅረት ፈቃድ የተሰጣቸውን ተማሪዎች ከመሸለም አያግድም።

4. ከትምህርት መቅረት ምን ማለት እንደሆነ መወሰን

   a) ለሪፖርት ማድረግ ዓላማ፣ MCPS ከትምህርት ቤት መቅረትን የሚገልጸው በሜሪላንድ የተማሪ ሪኮርድ መመሪያ ሥርዓት ፍቺ መሠረት ተማሪዎች በትምህርት ላይ «የሌሉበት ቀናት» ናቸው።

   b) አንድ ተማሪ በአካል በክፍል ውስጥ ካልሆነ(ች) ነገር ግን MCPS ቀጥተኛ ክትትል በሚያደርግበት ሁኔታ ትምህርት ላይ ሲሆን/ስትሆን፣ ተማሪዎች ለስቴት እና ለአካባቢው በትምህርት ላይ መሆናቸውን ሪፖርት ለማድረግ እንደ ተገኙ ይቆጠራሉ። ነገር ግን፣ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ አለመኖራቸውን አስተማሪው(ዋ) ይመዘግባል/ትመዘግባለች። በስቴት እና በአካባቢ ሪፖርቶች ላይ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ እንዲረዳ ቀሪዎችን ተቆጣጣሪ ጸሐፊ ተግባራዊ የሆነ መለያ ኮድ ይሰጣል/ትሰጣለች። በዚህ ብቻ ባይወሰንም ይህን የመሳሰሉ የመቅረት ምሳሌዎች፡-

      (1) በ MCPS ከክፍል ውጪ በሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች እንደ በጎ ፈቃደኛ ተማሪ የረዳትነት አገልግሎት መስጠት

      (2) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ተሳትፎ

      (3) የተማሪዎች የአመራር ስብሰባ

      (4) የመስክ ጉዞ

(5) የጤና ክፍል ጉብኝት

(6) ጊዜያዊ የማስተማር አገልግሎቶች

(7) በት/ቤት ውስጥ ሆኖ ከክፍል መታገድ

d) ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ ለተራዘመ ጉዞ በወላጅ/አሳዳጊ ከትምህርት ቤት የቀሩ ተማሪዎች ከት/ቤት እንደለቀቁ ይቆጠራል፥ እና በሚሄዱበት የተማሪው(ዋ)ን ትምህርት የመቀጠል ሀላፊነት መወጣት እንደሚጠበቅባቸው MCPS ለወላጅ/አሳዳጊ ማሳወቅ አለበት።

e) ተማሪው(ዋ) ወደ ት/ቤት በተመለሰ(ች) በሦስት ቀን ውስጥ ከወላጅ/ሞግዚት/ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ የሚቀርብ የእያንዳንዱን የቀረ(ች)በትን ምክንያት የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ ያስፈልጋል።

f) ዘግይተው የሚመጡ ወይም ከት/ቤት ቀደም ብሎ የሚለቀቁ ጥያቄዎች በወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ መሆን አለበት።

g) “ብቁ ተማሪ” ምን ማለት እንደሆነ "MCPS ደንብ JEA-RB" ላይ ተገልጿል፣ ስለ ተማሪዎች ትምህርት ቤት መግባት ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ስለመቅረት ማስታወሻ ማቅረብ እና አርፍዶ ስለመምጣት እንዲሁም በትምህርት ሠዓት ቀድሞ ስለመውጣት ጉዳይ ኃላፊነት መውሰድ ይችላል/ትችላለች። ርእሰመምህር/ተወካይ ብቁ ስለሆነ(ች) ተማሪ የሚከተለውን በጽሑፍ ለወላጅ/አሳዳጊ የመግለጽ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

1) ብቁ ተማሪዎች የሚቀሩበትን/የቀሩበትን ምክንያት የራሳቸውን ማብራሪያ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ።

2) በህገ ወጥ መንገድ መቅረት ላይ ማንኛውም አስተዳደራዊ ክትትል የሚደረገው ብቁ በሆነ ተማሪ ላይ ነው። በተጨማሪ ተማሪው(ዋ) ከወላጅ/ሞግዚት ጋር በጥገኝነት የሚኖር/የምትኖር ከሆነ ሳይፈቀድ የመቅረቱ(ቷ) ሁኔታ ለወላጅ/ለአሳዳጊ ይገለፃል።

## V. *ይግባኝ*

MCPS ደንብ KLA-RA፣ ከህዝብ ለሚመጡ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት፣ የርእሰመምህሩ/የተወካይ ውሳኔ ይግባኝ የማለት ሂደቶችን ይደነግጋል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** የሜሪላንድ ደንብ ኮድ፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-301.1፤ የሜሪላንድ መተዳደሪያ ደንቦች§13A.03.02.08B (4) እና §13A.08.01.01–07፤ MCPS የሀይማኖት ልዩነቶችን ስለማክበር መመሪያዎች፤ የተማሪ መብቶች እና ሀላፊነቶች መመሪያ፤ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ስነምግባር ደንብ

***የዚህ ደንብ ታሪክ፡-*** የቀድሞ ደንብ ቁጥር 515-1፣ ሴፕቴምበር 12, 1980 (ማውጫው ተሻሽሏል)፣ ዲሰምበር 1986 ተሻሽሏል። አክቶበር 28 ቀን 1993 ተሻሽሏል። ኦገስት 19 ቀን 1997 ዓ.ም ተሻሽሏል፣ ኖቨምበር 3 ቀን 2005 ተሻሽሏል፣ ሜይ 12 ቀን 2010 ተሻሽሏል፣ አክቶበር 7 ቀን 2013 ተሻሽሏል፣ ፌብሩዋሪ 4, 2014 ተሻሽሏል፣ ሴፕቴምበር 11, 2014 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 6, 2015 ተሻሽሏል፣ ፌብሩዋሪ 9, 2018 ተሻሽሏል፣ አክቶበር 8, 2019 ተሻሽሏል።ኤፕሪል 28, 2022 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 5, 2022 ተሻሽሏል፣ አክቶበር 17, 2023 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጅንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024